# መግቢያ

I. ሀገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት አመታት በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በፖለቲካዊ መስኮች በርካታ አዎንታዊ ለውጦችን አስመዝግባለች። እነዚህን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ለውጦች አስጠብቆ ለማስፋት፣ ስህተቶችን ለማረም እንዲሁም የዛሬውንና የመጪውን ትውልድ ጥቅምና ፍላጎት በዘላቂነት ለማሟላትና ሕብረ-ብሔራዊ አንድነትን ለማጠናከር የኢህአዴግ አባልና አጋር ድርጅቶች ወቅቱ ለሚጠይቀው ትግል በሚመጥን መልኩ ለመደራጀት አምነው የፈፀሙትን ውህደት መነሻ በማድረግ ይህ የ"ብልጽግና ፓርቲ" ፕሮግራም ተዘጋጅቷል።

II. በሀገራችን ተጠብቀው መስፋት ያለባቸው በርካታ ድሎች ተመዝግበዋል። በኢኮኖሚው መስክ ሀገራችን ለተከታታይ ዓመታት ያስመዘገበችውን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት፣ የድህነት ቅነሳ፣ የመሰረተ ልማትና የማህበራዊ አገልግሎት መስፋፋት ግለቱን ጠብቆ እንዲቀጥል ማድረግ ያስፈልጋል። በፖለቲካው መስክ የተዘረጋው የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እኩልነትን ሊያረጋግጥ የሚችል ህገ-መንግስታዊ ፌዴራላዊ ስርዓት ጉድለቶቹን አርሞ መሄድን ይጠይቃል። በውጭ ግንኙነት መስክ ሀገራችን በዓለም አቀፍ መድረክ የፍትህና የገለልተኝነት ተምሳሌት መሆኗን አስጠብቀን መዝለቅ ይጠበቅብናል።

III. በሌላ በኩል ባለፉት ዓመታት የታዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ስህተቶችን ያለማወላወል ማረም ያስፈልጋል። አሁን ሀገራችን በደረሰችበት የዕድገት ደረጃ ከዚህ በፊት በተከተልነው የልማት ፋይናንስ ሞዴል በኢኮኖሚና ማህበራዊ መስክ ያስመዘገብነውን ዕድገትና ልማት በተመሳሳይ መንገድ አስጠብቆ ማስቀጠል ከባድ

ፈተና የሆነበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። ያስመዘገብነውን የኢኮኖሚ ዕድገት አንድም የዕድገት ምንጮችን በማስፋት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በመንግስት ጉድለት ምክንያት የተፈጠረውን የሀገር ሀብት ብክነትና ዝርፊያ በመከላከል፣ የሀገራችንን ህዝቦች ፍትሃዊና የላቀ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በመሆኑም ምርታማነትን የሚያሳድግና በግሉ ባለሀብትና በመንግስት ትብብር የሚገነባ የኢኮኖሚ ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል። የግሉ ባለሀብት በሀገራችን ውስጥ በቂ ሀብት የሚፈጥርበትንና ምርታማነት የሚያድግበትን የፋይናንስ ሞዴል መከተል ይጠይቃል።

በፖለቲካው መስክ የብሔር ማንነትን እና ሀገራዊ ማንነትን፤ አጣጥሞ በዘላቂነት የሚያስኬድ የሀገርና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ማካሄድ ያስፈልጋል። ህብረተሰብን በጎራ በመክፈል አግላይ የነበረው አካሄድና አደረጃጀት አቃፊና አካታች ሆኖ የሀገራችንን ተጨባጭ የፖለቲካ ችግር በሚፈታ ማእቀፍ ሊሻሻል ይገባል። የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ዕንቅፋት የሆኑ ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶች ከዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች የላቁ ናቸው የሚለው ምሉዕነት የጎደለው ትንተናና የፖለቲካ ፕሮግራም፣ ሀገራዊ ሁለንተናዊ ብልጽግናን በሚያስቀድሙ የፖለቲካ ዕይታዎች መተካት ይኖርበታል። የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲያችን መቀጨጭ ታርሞ ግልጽና ለሁሉም የሀገራችን ህዝቦች የዴሞክራሲ ስርዓት ማሳያ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል።

IV. ሀገራችን ኢትዮጵያን የአሁኑንና የመጪውን ትውልድ ጥቅምና ፍላጎት የሚያስከብር አስተማማኝ መሰረት ዛሬ ላይ በመገንባት ሰላም፣ ዴሞክራሲ፣ ህብረ-ብሄራዊ አንድነት፣ የዜጎች ክብር፣ ፍትህ እና የጋራ ብልጽግና የተረጋገጠባት ሀገር መሆን ይኖርባታል። ኢህአዴግ በትጥቅ ትግል ለድል ከበቃ በኋላ ለ28 ዓመታት ሀገርን በመራበት ታሪኩ የተንቀሳቀሰበት ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ አውድ ተለውጧል። በተያያዘም ኢህአዴግና አጋር ድርጅቶች ሲከተሏቸው የነበሩ የርዕዮተ ዓለም

ዕሳቤዎች ፖለቲካዊ አዋጪነታቸው መንምኗል፡፡ ፓርቲያችን ከዘመናዊ የፖለቲካ ጨዋታ ህግጋት ጋር ተናቦ የሚሄድ የዕይታ ለውጥ በአጭር ጊዜ በማካሄድ እየተለወጠ ካለው ምህዳር ጋር መዋጀት እና እንደ ሀገርም ከፍተኛ ጥፋትን ሊያስከትል ከሚችል የቆሞ ቀርነት አዙሪት ውስጥ መውጣት ወሳኝ ነው፡፡

V. በጥቅሉ ሀገራችን በኢህአዴግ አመራር በቆየችባቸው ዓመታት የነበሩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ድሎችን ጠብቆ ማስፋት፣ ጉድለቶችን ነቅሶ በማውጣት ያለማወላወል እንዲታረሙ ማድረግ እና የዛሬውንና የመጪውን ትውልድ ጥቅምና ፍላጎት ማሟላት ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም ግን በቀድሞ ኢህአዴግና አጋር ድርጅቶች ቅርጽና ይዘት እነዚህን ድሎች ጠብቆ ማስፋት፣ ስህተቶችን ማረም እና የመጭውን ትውልድ ጥቅም የማስከበር አላማዎችን በተሟላ መልኩ ማሳካት አይቻልም፡፡ በመሆኑም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችን እና አጋር በሚል ሲጠሩ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶችን በማካተት፣ አቃፊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ስርዓት የሚገነባ “የብልጽግና ፓርቲ” በሚል ስያሜ ህብረ-ብሔራዊ ፓርቲ ማቋቋም አስፈልጓል፡፡

VI. ወጥ ዓላማ ያለው ህብረ-ብሔራዊ ውህድ ፓርቲ መሆን ሰፊውን የሀገራችንን የህዝብ ክፍል የሚያቅፉ ነገር ግን በዕይታ ግድፈት ከሀገራዊ የፖለቲካ ውሳኔ የተገለሉትን ኢትዮጵያዊያን በእኩልነት የሚሳተፉበትን ፓርቲያዊ አወቃቀር ለማምጣት ያስችላል፡፡ በሌላ በኩል ህብረ-ብሔራዊ ፓርቲው አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን ብሔሮች በሚያሳትፍ እና በሚያካትት መልኩ ውክልና እና ብቃትን መሰረት ያደረገ የውሳኔ አሰጣጥ ስርአትን በማጠናከር በሃሳብ ልዕልና ላይ የተመሰረተ ዘመናዊ የፖለቲካ ፉክክርና ትብብር መሰረት እንዲይዝ በማድረግ ሀገራችን የተያያዘችው ዴሞክራሲያዊ የለውጥ ሂደት ቀጣይነት ኖሮት ከማይቀለበስበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ እና እንዲጠናከር የሚያግዝ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ እውነተኛ ህብረ-ብሔራዊ የሆነው

ውህድ ፓርቲያችን የአላማና የተግባር ውህደት በማምጣትና የተሻለ ኃይል በማሰባሰብ በቀጣይ ለላቀ የዓላማ አንድነትና ሀገራዊ ድል የሚያበቃ እንዲሁም የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልጽግናን የሚያረጋግጥ አቅጣጫ የሚከተል ይሆናል።